ጉዳዩ: የተጠናከረ - የተማሪ ጤናማነት፣ ደህንነት እና ጥበቃ እርምጃዎች፣ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት

ውድ የACPS ቤተሰቦች፣

ማግኘት-የሚገባችሁን ዕረፍት፣ በዚህ በጋ (summer) እያገኛችሁ-እየተደሰታችሁ እና፣ ለአዲሱ የትምህርት ዓመት፣ እየታደሳችሁ እና ዝግጁ-ሆናችሁ መሆኑን ተስፋ-እናደርጋለን። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የ2022-23 የትምህርት ዓመትን ለመጀመር - ተማሪዎቻችንን፣ ሠራተኞችን እና ቤተሰቦችን ተመልሰው ሲመጡ-እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ጓጉተናል። የትምህርት ቤት በሮቻችንን ለመክፈት እና ወደ ማስተማር እና መማር ለመመለስ፤ በጠንካራ-ስራ እየተዘጋጀን ነው። ዋና-እሴታችንን የሆነውን - ሁሉን-ተቀባይነት ለመጠበቅ፤ የዚያ ዝግጅት-አካል ሆኖ የሚካተተው፤ በተማሪ ጤናማነት፣ ደህንነት እና ጥበቃ መረጋገጥ ላይ ትኩረት በመስጠት፣ ተማሪዎች በደስታ-የሚቀበሏቸው እንዳላቸው፣ እገዛ-የሚያገኙበት እና ደህንነት-ያለበት ስሜት - በሁሉም የትምህርት ቤት ህንፃዎቻችን ውስጥ እንዲሰማቸው በማካተት ያተኮረ ነው። ይህ፣ ግንኙነቶችን ከተማሪዎች ጋር በማሳደግ፣ እና ያለንን ትኩረት - በማህበራዊ፣ ስሚኢታዊ እና የቀለም ትምህርት ላይ በማድረግ፤ በመጨረሻይ ይህ-ሁኔታ የተሻሻለ ባህሪይ እና የደህንነት ውጤቶችን ለማስገኘት ወሣኝ ነው።

ይህ ዳር-ለማድረስ፤ ለትምህርት ዓመት መጀመሪያ-ሆኖ - እነዚህን ጠቃሚ-የሆኑ የተማሪ ጤናማነት፣ ደህንነት፣ እና ጥበቃ አዲስና ማሻሻያ (updates) እና ማስታወሻዎችን፤ ከእናንተ ጋር ማጋራታችን በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

| ርዕስ/የጉዳዩ-ዓይነት | የትምህርት ቤት ደረጃ | መረጃ |
| --- | --- | --- |
| **ማህበራዊ እና ስሜታዊ እገዛዎች - ለተማሪዎች** | የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከK-8 እና ሁለተኛ-ደረጃ | እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፤ ለእርሱ-ብቻ የተወሰነ-ጊዜ ያለው፣ ተማሪዎች ዕለታዊ የማህበራዊ-ስሜታዊ ትምህርት (social-emotional learning)ን የሚያገኙበት 30 ደቂቃዎች ይኖሯቸዋል። እንደ ማህበረሰብ ዙሪያ (community circles) ያሉ መዋቅሮች፣ የRULER ስርዓተ ትምህርት ከ'የል ማዕከል - ለስሜታዊ ማስተዋልና ግንዛቤ (Yale Center for Emotional Intelligence)' የቀረበውን ለማሰራጨት፣ እና አዎንታዊ የሆነ የባህሪይ ጣልቃ-ገብነቶችን እና እርዳታዎችን ለማጠናከር፣ ጥቅም-ላይ ይውላል። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪ እርዳታ ቡድን (Student Support Team) በበኩሉም፤ የበለጠ ዒላማ-ያደረገ እና ጠንከር-ብሎ የሚሰጡ የአነስተኛ-ቡድን (small group) እና የእያንዳንዱ-ግለሰብ ጣልቃገነነቶች (individual interventions)ን፤ በባለብዙ ደረጃዎች የስርዓት እገዛ (Multi Tiered System of Support) (INSERT MTSS LINK HERE) ሂደት አማካኝነት፣ በዚህ ተለይተው-ለወጡ ተማሪዎች ይሠጣል። በተጨማሪም - የDevereux Student Strengths Assessment (DESSA)ን - የማህበራዊ-ስሜታዊነት መሣሪያን በመጠቀም፤ የየግል እና በጋራ-በአንድነት በመሆን፣ ጠንካራ-ጎኖችን ለመለየት እና ለማሳደግ - ተማሪዎች ይገመገማሉ። |
| **ቴክኖሎጂ እና ግንኙነቶች (Communications)** | የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከK-8 እና ሁለተኛ-ደረጃ | በመደበኛነት የጊዜ-ሰሌዳ የተሰጣቸው - የመከላከያ ጥበቃ የሕዝብ ማስታወቂያ (public announcement (PA) ዘዴዎችን፣ እና የስልክ ስርዓት ዘዴዎች፣ በበጋ (summer) ወቅቱ ውስጥ ተከስተዋል፤ እና በዓመቱ ውስጥ - የትምህርት ቤት የመገናኛ ስርዓት ዘዴዎች እንዲቀየሩ ተደርጓል። በተጨማሪነትም፤ የስልክ-ማገናኛ አገልግሎት (cellular service) በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS)፣ የኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King St. Campus) ዙሪያ ተስፋፍቷል። |

| | | |
|---|---|---|
| **በግልጽ-የተመደበ - የተማሪ እና የሠራተኛ መግቢያዎች** | የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከK-8 እና ሁለተኛ-ደረጃ | እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፤ ለተማሪ፣ ሠራተኛ እና ጎብኚ-እንግዳ መግቢያ የሆነውን ልዩ መግቢያዎች ይመድባል። ይህ ልምድ፤ ወደ ተቋሙ ለመግባት ያለውን ሁኔታ በተሻለ-ሁኔታ ለመቆጣጠር ያስችላል። |
| **ዝግ-የሆነ ካምፓስ (Closed Campus)** | የመጀመሪያ ደረጃ፣ ከK-8 እና ሁለተኛ-ደረጃ | ለሁሉም ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ማህበረሰብ አባላቶች - እንደማስታወሻነት ለማቅረብ፤ የACPS ካምፓሶች ዝግ-የሆኑ ካምፓሶች (closed campuses) ናቸው። "ዝግ-የሆነ ካምፓስ (Closed Campus)" ማለት፤ የምሣ ሰዓትን ጨምሮ፣ ተማሪዎች ፈቃድ-ካላገኙ በስተቀር መምጣት እና መሄድ አይፈቀድላቸውም። ቀደም-ብሎ የመለቀቅ (early dismissal) ሁሉም መስፈርት፣ በትምህርት ገበታ-መገኘት ቢሮዎች (attendance offices) አማካኝነት ክትትል እንዲደረግ ያስፈልጋቸዋል። በትምህርት ቀኑ ውስጥ - በትምህርት ገበታ-መገኘት ሕግ የሚጠይቀውን መስፈቶችን ባለመከተል ካምፓሱን ለቅቀው የሚሄዱ ማንኛውም ተማሪዎች፤ ከትምህት ቤቱ አስተዳደር  ጣልቃ-ገብነቶች ጋር ይዳረጋሉ። |
| **አዲስ ተማሪ፣ የመታወቂያ (ID) መስፈርቶች** | ሁለተኛ-ደረጃ | ተመራጭ-የሆነ የደህንነት-ጥበቃ ተሞክሮን በስራ-ላይ ለማዋል በሚደረግ ጥረት ውስጥ፤ ሁሉንም በሁለተኛ-ደረጃ (በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ውስጥ ያሉ ተማሪዎች - በየቀኑ የተማሪ መታወቂያቸውን ይዘው እንዲገኙ እንጠይቃለን። ይህ ልምድ፤ በትምህርት አሰጣጡ ሰዓታት ወቅት፣ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ ካምፓስ ውስጥ ለመግባት እንደሚችሉ - የህንፃው አስተዳደሮች እና የጥበቃ-ሹሞች ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።<br><br>የዲጂታል የተማሪ መታወቂያ (digital student identification (ID) የሙከራ ፕሮግራምን፣ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች ውስጥ እያደረግን ነው፤ ይህ ፕሮግራም ተማሪዎች የተለመደውን ዓይነት ወይም የዲጂታል መታወቂያ (digital Id)ን - (በስማርትስልክ/ስማርት ዲቫይስ ላይ የተቀመጠውን) በትምህርት ቤት የመግቢያ ቦታ ላይ ስካን (scan) በማድረግ ለመጠቀም ያስችላቸዋል። በትምህርት ቤት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት-ሣምንታት ውስጥ፣ የዲጂታል የተማሪ መታወቂያ (digital student ID) የሙከራ-ማስጀመሪያ ፕሮግራም ይካሄዳል።  የዲጂታል መታወቂያ (digital ID) በግዴታ-መኖር የሚገባው ነገር አይደለም፤ እና ተገቢ የሆነውን የትምህርት ቤት አስተዳደሮች በማሳወቅ፣ ተማሪዎ ከዲጂታል መታወቂያ (digital ID) ፕሮግራም እንዲወጣ (opt out እንዲያደርግ) - ማድረግ ይችላሉ።  መታወቂያዎችን (IDs)ን ለማግኘት/እንዲሰራ-ለማስጀመር (activating) የሚጠቁሙ መረጃዎችን፣ በሌላ - ለቤተሰቦች እና ተማሪዎች ከACHS አመራሮች በሚሰጥ ግንኙነት (communication) ውስጥ ይጋራላችኋል። |
| **የትምህርት ቤት የጥበቃ-ሹሞች (School Security Officers)** | ሁለተኛ-ደረጃ | የትምህርት ቤት አስተዳደሮችን ለማገዝ፤ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቦታዎች - ተጨማሪ የትምህርት ቤት የጥበቃ ሹሞች (school security officers (SSOs) ያገኛሉ። |
| **መጨናነቅን-የቀነሰ የመለቀቂያ-ጊዜ (Staggered Dismissals) በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች** | የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች | በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - ኪንግ ስትሪት (King Street) እና ሚኒ ሃዋርድ (Minnie Howard) ካምፓሶች ውስጥ፣ በቀለም-ትምህርት ዓመት 2022-23 ሙሉው-ጊዜ ውስጥ - በመለቀቂያ ሂደት ላይ የሚፈጠሩ |

| | | |
|---|---|---|
| | | መጨናነቆችን በመቆጣጠር ይጠብቃል። ይህን ልምድ በ2021-22 የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ በተሳካ-ሁኔታ በማስፈጸም፤ በዚያን-ጊዜ ተቋሙን ለቀው-የሚሄዱ ተማሪዎችን ቁጥር በመቆጣጠር፣ በተቋሙ የሚፈጠሩ የተማሪ ብዛት መጨናነቅን ቀንሷል። |
| **የትምህርት-አሰጣጥ ቀን ሎጂስቲክ - ለከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች** | የከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች | በሁሉም የACHS ካምፓሶች የሚገኙ የአመራር ቡድኖች፣ የትምህርት-አሰጣጥ ቀኑን ሎጂስቲክስ ላይ ምልከታ-ያደረጉ እና፣ ቀጣይነት ያለው የደህንነት-ጥበቃ መሻሻልን የሚያግዙ ለውጦችንም አድርገዋል።<br><br>በሚኔ ሃዋርድ (Minnie Howard) እና በኪንግ ስትሪት (King Street) ካምፓሶች ውስጥ፤ አሁንም-ቢሆን - ተማሪዎች እስከ ስምንት ክፍሎች የጊዜ-ሰሌዳዎች ይኖሯቸዋል። ለምሣ የተመደበው ጊዜ፤ በካምፓሱ ውስጥ በተወሰኑ ቦታዎች ግደባ-የተደረገበት እና፣ ተማሪዎች ምሣ እንዲበሉ፣ በማህበራዊ-ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት እንዲሳተፉ፣ በአማካሪ-ክፍለጊዜዎች (advisory periods) ውስጥ እንዲካፈሉ፣ እና በክለብ እና ድርጅቶች ውስጥ አንዱ-አካል እንዲሆኑ ጨምሮ ያከናውናሉ። ለምሣ የተመደበው ጊዜ ውስጥ፣ በካምፓሶቹ ዙሪያ እና፣ በካምፓሱ-ውስጥ የውጪ የመመገቢያ ቦታዎችን ጨምሮ፣ እንዲሁም የተማሪ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፣ የሠራተኛ-ቁጥጥር ይደረጋል።<br><br>በበርካታ ካምፓሶች ውስጥ ክፍሎችን የሚወስዱ ማንኛውም ተማሪዎች፣ በACPS የመጓጓዣ አገልግሎት አማካኝነት ይጓጓዛሉ። ተማሪዎች ቀደም-ብለው ሊሄዱ የሚችሉበት ወይም አርፍደው ወደ ትምህርት ቤት መምጣት የሚችሉበት ብቸኛ-ጊዜ፤ በቅድሚያ-ፈቃድ ያገኘ የጊዜ-ሰሌዳ ከኖራቸውና - ቀደም-ብሎ መለቀቅ ወይም አርፍዶ መምጣትን የሚያስችል ካላቸው (ማለትም፤ ምንም-የጠዋት ወይም ከከሰዓት በኋላ ክፍሎች ከሌሉ) ነው። |
| **የሠራተኛ የመታወቂያ-ወረቀት (ID) አስፈላጊነት** | ሁሉም፣ የክፍል (division) ሠራተኛ | እንደማስታወሻ-ሆኖ፤ ሁሉም የ'ACPS' ሠራተኞች - በትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በማዕከላዊ ቢሮ፣ እና/ወይም በACPS-ንብረት በሆኑ ቦታዎች ውስጥ፤ የስም-ባጅ (badge) እንደሚታይ አድርገው ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ይህ ተመራጭ-የሆነ ልምድ፣ አስተዳደር እና የትምህርት ቤት የጥበቃ-ሹሞች፤ በትምህርት ቤቱ ተቋሞች ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ፣ በቀላሉ - ሠራተኞችን ወይም ጎብኙ-እንግዶችን ለመለየት ያስችላል። |

የትምህርት ዓመቱ እየተካሄደ በሚቀጥልበት ጊዜ፤ ተጨማሪ እርምጃዎች ዋስትና-እንደተሰጣቸው የሚፈጸሙ ሲሆን፣ እና ወደ ቤተሰቦች፣ ሠራተኞች እና ማህበረሰቡ ግንኙነት በማድረግ እንዲያውቁት ይደረጋል። በተጨማሪም፤ የትምህርት ቤት ሕግ ማስከበሪያ አጋርነት (School Law Enforcement Partnership (SLEP) - አማካሪ-ቡድን፣ በበጋ (summer) ወቅት-ጊዜ ውስጥ ሁለት ጊዜ የተገናኘ ሲሆን፣ እና ይህንንም በመጪው ወራቶች ውስጥ ማድረጉን ይቀጥላል። በ'SLEP advisory group' ላይ የሚሰጡ-አዲስና ማሻሻያዎች (updates) እዚህ ማግኘት ትችላላችሁ: SLEP Advisory Group. በአሁኑ-ጊዜ፣ የ'school resource officer (SRO)' ፕሮግራም፣ በስራ-ላይ ሆኖ እስከ ጁን (June) 30 ቀን 2023 ድረስ ይቀጥላል።

**እናንተ፣ ከእኛ ጋር እንዴት አጋርነትን መፍጠት ትችላላችሁ?**

ወደዚህ አዲስ የትምህርት ዓመት በምንገባበት ጊዜ፣ የእናንተን አጋርነት - አድናቆት እንሰጠዋለን። የተማሪዎቻችን፤ ጤናማነት፣ ደህንነት እና ጥበቃን በማረጋገጥ ላይ፣ በትምህርት ቤት ማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ-ሰው የሚጫወቱትን ሚና፣ እውቅና-እንሰጠዋለን። ጥረቶቻችንን ልታግዙ-የምትችሉት፤ በACPS ተማሪ ጤናማነት፣ ደህንነት እና ጥበቃ እርምጃዎች ላይ እራሳችሁን በቅርብ-

ጊዜ መረጃ እያጎለበታችሁ፤ ተማሪያችሁ እና ቤተሰቡ - በሁሉም መስፈርቶች ተገዢ መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ እና ሊኖሯችሁ የሚችሉ ማንኛውም ስጋቶችን ከትምህርት ቤት ሹሞች ጋር በማጋራት ነው።

በዚህ በልግ (fall) ሁሉም ተማሪዎቻችን ተመልሰው ስናገኛቸው-ደስታ ይሰማናል፣ እና ሁሉን-ተቀባይ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጥበቃ-የተደረገለት - የመማሪያ አካባቢን በማቅረብ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲበለጽጉ ለማድረግ በቁርጠኝነት እንሠራለን። አዲሱን የትምህርት ዓመት - ለማስተማር እና ለመማር በምንጀምር ጊዜ፤ በቀጣይነት ለምታሳዩት ትብብር፣ እናመሰግናለን።

ከሰላምታ ጋር፣

ዶ/ር ግሪገሪ ሲ. ሃችሂንግስ (Dr. Gregory C. Hutchings, Jr.)
የትምህርት ቤቶች ጠቅላይ-ሥራ አስኪያጅ